# “እንቁጣጣሽ!” ለመባባል ያብቃን!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

ዘመን ሲለወጥ በጦቢያ ወንዙ፣ ሜዳው፣ ሸለቆው ጋራውና ተራራው አዲስ መልክ፤ ለየት ያለ ውበትና መአዛ ይዞ ይታያል። ወንዙ እየጠራረገ ከአገር የሚያስወጣውን ለም አፈር ይዞ ከመግበስበስ ይታቀብና ፈካ ብሎ እያፏጨጨ መጓዝ ይጀምራል። የእርሻ ቦታውም ሌት ከቀን በሚፈጋው፤ ነገር ግን ሰርቶ በማይጠራቅምለት ገበሬ መታረሱ ቀዝቀዝ ይልለትና በለመለመና ባማረ የሰብል ቡቃያ ተሸሞንሙኖ ህይወት ያለውን ነገር ሁሉ ቀልብ መሳብ ይጀምራል። ተራራውና ጋራው እንደዚሁ በአደይ አበባ፣ በሶሪትና በሌሎችም ህብረ-ቀለማት በሆኑ ተክሎች ተሸቆጥቁጦ አይንን ይማርካል፤ መንፈስንም ያድሳል። አዎ ምድር በጠቅላላው ሳትፈልገው ሲወድቅባት የከረመውን አረም፣ ገለባ፣ እሳት፣ ግፍ፣ መከራ ወዘተርፈ ጠራርጋ ታስወግድና አዲስ ምኞት፣ አዲስ ተስፋ ይዛ፤ አዲስ ልብስ ለብሳ፣ በብርሃን ፍንትው ብላ አዲስ አመትን ትቀበላለች።

እንስሳት በበኩላቸው አዲሱን አመት የሚቀበሉበት ሥርዓት አላቸው። ወፎች ተደብቀው ከከረሙበት ቤት ብርር ብለው እየወጡ ቺው-ቁ-ቁቺቺው... እያሉ ይዘምራሉ፤ በሰማዩ ክንፋቸውን ይዘረጋሉ፤ በምድሩም ይበተናሉ። ከብቶች ተጨማዶ የከረመው ቆዳቸው ይፍታታና በመስክ ላይ ተሰማርተው ንጹሕ አየር እየተነፈሱ ቡርፍ... ቡርፍ-ቡርፍ እያደረጉ የለመለመውን ሳር ይግጣሉ። ሜዳ ላይ ተጋድመው የመስከረምን ጸሐይ በቆዳቸው እየሞቁ ከሆድ ያስገቡትን ወደ አፍ እየመለሱ ያመነዥካሉ። እምቦሶቻቸው ወይም ውርንጮቻቸው ከወዲያ ወዲህ እየተራወጡ የከብቶችን ሰኞ-ማክሰኞ ጨዋታ ይጫወታሉ። ክረምቱ፣ ጳጉሜና መስከረም በለገሷቸው ግጦሽና ውሃ ርሃባቸውን አስታግሰው፣ ጥማታቸውን አርክተው ላሞችና እምቦሶች፤ እናት በግና ግልገሎች አንገት ላንገት ተቃቅፈው እየተላላሱ አዲሱን አመት በተስፋ፣ በደስታና በፌስታ ይቀበላሉ።

ሕዝብ እንደዚሁ ዘመንን የሚቀበልበት ወግና ባህል አለው። ሴቶች ልጆች በአደይ አበባና በሶሪት የተሸቆጠቆጠ የእንግጫ ጉንጉን አንገታቸው ላይ ደርድረው፣ በጠልስም፣ በመስቀል፣ በዲሪ፣ በአናባርና በአልቦ እየተዋቡ፣ አበባየሁ- ሆይን እየዘመሩ አዲሱን አመት ይቀበላሉ። ወንዶች ልጆች እንደዚሁ ችቧቸውን እያበሩ፣ ሆያ-ሆየን እየጨፈሩ፣ ገናና ምክት እየተጫወቱ አዲሱን አመት በደስታና በፌስታ ይቀበላሉ። እናቶች፣ ጎልማሳሶችና ሽማግሌዎች ሳይቀር አመቱን ሙሉ የፈጸሙትን ስህተት ወይም የደረሰባቸውን ግፍና ፍዳ በጳጉሜ ውሀ ሙልጭ አድርገው ታጥበው በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ እቅድ፣ በአዲስ ተስፋ አዲሱን አመት ይቀበላሉ። አዲስ አመት ሲመጣ ሕዝብ ከቻለ አዲስ ልብስ ካልቻለ ደግሞ ያለችውን ጥቢቆ በእንዶድና በአመድም ቢሆን እሽት አድርጎ አጥቦ በአዲስ መንፈስ ለአዲስ አመት ይዘጋጃል። ችቦውን አብርቶ “በቆላ በደጋ ያላችሁ እንዴት ከረማችሁ” እያለ  ለአገሩ ለወገኑ መልካም ምኞትን ይገልጻል።

በአዲስ አመት አዲስ መንፈስ ይዞ ሲነሳ ጭራሽ የማይታየው ግፍኛ አገዛዝ ነው። ዘመን ተቀየረም አልተቀየረም የግፈኛ አገዛዝ መሪ ተዋንያን የሚረኩት ሕዝብ በችጋርና በበሽታ እንደ ቅጠል ሲረግፍ እነርሱ ብር በጆምላ በጆምላ ሲቆጥሩና ከወንበር ላይ ሙጪጭ ብለው ሲቀሩ ነው። አዎ ግፈኛ አገዛዝ እንኳን አንድ፤ መቶ ጳጉሜዎችም ተደራርበው አንድ ላይ ቢመጡ ራሱን ዞር ብሎ ለመፈተሽ፣ ሐጥያቱን ለማጠብ ወደ ወንዝ እንዳይሄድ የተሰራበት ድርና ማግ አስሮ ገንዞ ይይዘዋል። ይህም በመሆኑ ግፈኛ አገዛዝ ብዙም ተለይቷት በማያውቀው ጦቢያ የግፈኛ አገዛዝ ቆሮዎች ግፍ-ተቀባይ ላቡን አንጠፍጥፎ በገነባው እልፍኝና አዳራሽ በሳቅ በጭፈራ አዲሱን አመት ሲያሳልፉት ልጁን፣ ወላጁን ወይም ዘመድ አዝማዱን የገደሉበት፤ በጨለማ ቤት ያጎሩት፤ ከመንገድ ዳር ያፈኑት፣ ከስራ ያባረሩት፣ ያሰደዱት፣ ንብረቱን የቀሙት በለቅሶና በእንባ እንቁጣጣሽን ያሳልፋል። እንዲህ አይነቱ ሐጥያት በጦቢያ ምድር እንኳን በአንድ በሰላሳና በአርባ ጳጉሜዎችና መስከረሞችም አልታጠብ ብሏል። እንዲያውም ይህ ሐጥያት አንዱ መስከረም ተምዘግዝጎ አልፎ ሌላኛው በመጣ ቁጥር እየበረታና እየከፋ ሄዱል።

ዛሬም አዲሱን ዘመን የምንቀበለው በሌላው አለም ሕዝብ ለሽርሽር ወደ ጨረቃ በሚሄድበት ዘመን በኛ አገር በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ የሚልሰው የሚቀምሰው አጥቶ እየረገፈ ባለበት ወቅት ነው። አዎ ዛሬም ሁለት ሺህ አንድ የምንለው ባልሰራው ሐጥያት ስንቱ ተገድሎ፣ አለም በቃኝ ውስጥ ታጉሮ፣ ለስደት ተዳርጎ፣ ንብረቱን ተቀምቶ፣ ከስራ ተባሮ ወዘተርፈ ባለበት ሰአት ነው። ደጋግመን ወደ አዲስ አመት ተሸጋገርን የምንለው ጋዜጠኛው የሕዝብን ብሶት ለመግለጽ ኮቢ በማንሳቱ እጁም ህሊናውም ታስሮ፣ ጠበቃውም ለተበደለ ጥብቅና በመቆሙ ፈቃዱን ተቀምቶ፣ ዘፋኙም የሕዝብን ስቃይ በማቀንቀኑ ከእስር ቤት ተወርዉሮ፣ ከግፍኛ ገዥዎች ጋር ያልቆመው ሁሉ በስለላ መረብ ተወጥሮ፣ የስሜት ህዋሳቱን ከጥቅም ውጪ አርጎ ባለበት ሰአት ነው። እርግጥ ነው ዛሬም “እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሳችሁ!” የምንባባለው ወንጀለኛ ሰው ከሳሽና ዳኛ፤ ተበዳይ ደግሞ ተከሳሽና ተከላካይ ሆነው ከወስላታ ፍርድ ቤቶች በሚቆሙበት

ሰዓት፣ አገርም ውስጧ ክልል በክልል ሆና ዳር-ድንብሯ ግን በውል አልታወቅ ብሎ በመኖርና ባለመኖር መካከከል ተወጥራ ባለችበት ወቅት ነው።

በእኔ እምነት በወርሃ መስከረምና ጥቅምት የሚንሿሿው ወንዝና ጅረት ድምጽ የሚስበው፣ አበባ የለበሰው ጋራ የሚማርከው፤ የከብቶች ፍንጥዝያ፣ የልጆች ጨወታ፣ የእናቶች፣ የጎልማሶችና ሽማግሎች ወግና ባልህ ሁሉ የሚያምረው፤ አዲስ አመትም በእርግጥ አዲስ አመት የሚሆነው ሕዝብ ከሚገድልና ከሚያሰቃይ አገዛዝ ተላቆ፣ኢፍትሐዊነትን በፍትህ ተተክቶ አዲስ ምእራፍ የተጀመረ እለት ነው። አለዚያ ግን በሃያ አንደኛው  ክፍለ-ዘመን ከጡት ያልተላቀቁ ሕጻናትን ጨምሮ በሰባና በሰማኒያ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በችጋርና በበሽታ እየተሰቃዬና እየረገፈ፣ እግዚአበሔር የለገሰው አእምሮ ተሸብቦ ከእውቀት ብርሃን ርቆ እንዲኖር መጋረጃ እየተጣለበት፣ በግፍ እየሞተ፣ እየታሰረ፣ እየተሰደደ፣ ንብረቱን እየተቀማ ባለበት ዘመን “እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሰህ” ብትሉኝ አዲስነቱ አይታየኝም።

ደስታን ቀርቶ ሐዘንን እንኳን መካፈል የሚያምረው በሐገር በመንደር ሰላም ሲሰፍንና በጎ ነገር ሲታይ ነው። እንኳን የእህል የሰው ዘር መፈጠሪያ ሆና ሳለ ጦቢያ ዛሬ የችጋር አርማ ሆናለች። ይህ የሚያሳየው በጦቢያ ምድር እንኳን አዲስ ዘመን ሊታይ ተገዳ የገባችበት ጨለማም ገና አለመንጋቱን ነው። እኔ በበኩሌ “እንቁጣጣሽ!” ሲሉኝ “በየአመቱ ያምጣሽ!” ብዬ ችቦዬን ይዤ የምወጣው  በጦቢያ ምድር ፍትህና ብልጽግና ሰፍኖ፣ ሳይፈልጉት ወንበር ላይ ጉብ ያለ ባለስልጣን ገዳይ፤ ዜጎቿ ደግሞ ባበሉ ባጠጡ ተገዳይ መሆናቸው ሲያከትም፣ ወላጅ ልጁን ልጅም ወላጁን ግብር እየገበረ የሚያንፈላስሰው ገኸ ገደለብኝ ወይም አፍኖ ወሰደብኝ እያለ እንባ ማፍሰሰ ሲያቆም ነው። እዎ ብችል ከልቤ “እንኳን አብሮ አደረስን!” የሚል መልስ መስጠት የምመርጠው ኢትዮጵያ የሚለውን ክቡር ቃል ከርሃብ መዝገበ-ቃላት ሊፍቅ የሚችል፣ ሕዝብን ከችጋርና በሽታ የሚያላቅቅ መርሃ ግብር የሚዘረጋበት ዘመን የመጣ ለት ነው። እስከዚያም ጸሎቴ “አዲስ ዘመን፣ አዲስ መስከርም በጦቢያ እንዲጠባ፤ በግፍና በመከራ የተበሳሳውን እርቃን የማይሸፍን ጥቢቆ አውልቃ አዲስ ልብስ ለመልበስ እንድትበቃ፤ በባእዳን እጅ ተቦክቶ በራሷ ልጆች የተዞረውን አቲቴና ውቃቢ እግዚአብሔር ሆይ እፍ ብለህ እንደ ጉም ጠራርግላት!” የሚል ነው። ምኞትና ተስፋዬም ጦቢያውያን በአንድነት ጸንተው፤ ፍትህ፣ ክብርና ብልጽግናን ተጎናጽፈው በቆሰለና በአረረ አንጀት ሳይሆን በእርካታ፣ በደስታና በፌስታ በተሞላ ልብ “እንቁጣጣሽ!” የሚባባሉበት አዲስ ዘመን ይመጣል የሚል ነው። ለዚያ ያብቃን! አሜን።

*ጳጉሜ ሁለት ሺህ ዓ.ም.*